# ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሴክሬተሪያት ፅ/ቤት የተሰጠ መግለጫ

በሞያሌ ከተማ በሚያዝያ 28/2010 ዓ/ም በተደራጀና በህቡእ ዝግጅት በተደረገበት የጥፋት ተልዕኮ በሁለት ጎራዎች የታጠቁ ኃይሎች መካከል ማሕበረሰብን ዒላማ ያደረገ በመጠኑም ሠፋ ያለ ግጭት ተከስቶ በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ድርሷል፡፡ በዚህ ግጭት የዜጎች ህይወት ጠፍቷል የመቁሰል አደጋም ደርሷል፡፡

በመላ ሃገሪቱ መንግስት እና የፀጥታ ኃይሎች ከሕብረተሰቡ ጋር በመሆን እያካሄዱ ባሉት ተከታታይ ስራና ጥረት ሠላምና መረጋጋት እየሰፈነ ባለበት በአሁኑ ወቅት በሕብረተሰቡ መካከል ግጭት እንዲፈጠርና ያለመረጋጋት እንዲሰፍን በሚሰሩ የሁከትና ብጥብጥ ኃይሎች ምክንያት ለደረሰው የዜጎች ህይወት መጥፋት ኮማንድ ፖስቱ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ይገልፃል፡፡ በዚህ ተግባር ላይ የተሳተፉና ከጀርባ ሆነው ድርጊቱን ሲመሩ የነበሩ አጥፊዎችን የመለየትና የማጣራት ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት የፀጥታ ሃይሎች ግጭቱን ያስቆሙት ሲሆን ሁኔታዎችም በመረጋጋት ላይ ናቸው ከዚህ በተጨማሪ በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር በስፋት እየተካሄደ መሆኑን ኮማንድ ፖስቱ ተገንዝቧል፡፡ እስከአሁን የፀጥታ ኃይሎች ባካሄዱት ጥብቅ ክትትልና በሕብረተሰቡ ጥቆማ በሚያዝያ ወር 2010 ዓ/ም ብቻ 142 ክላሽ፣ 88 ሽጉጥ፣ 17 የቡድን የጓላ ቀር መሳሪያዎች ፣ ከበርካታ ተተኳሾች ጋር እንዲሁም 11 የእጅ በምቦች በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

ይህ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ በሞያሌ ከተማም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች ለሚከሰቱ ግጭቶችና ለሚደርሰው ጉዳት ሰፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው፡፡

በመሆኑም በሞያሌ ከተማ የፀጥታ ኃይሉ ከመንግስት በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ትጥቅ የማስፈታት ሥራ እያከናወነ ሲሆን አስፈላጊው ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ሁሉ የተጠናከረ ትጥቅ የማስፈታት እርምጃ የሚቀጥል መሆኑን ኮማንድ ፖስቱ ያስገነዝባል፡፡

ህጋዊና ለራስም ሆነ ለአካባቢ ጥበቃ የሚውል ትጥቅ ያላቸው ዜጎችም ትጥቃቸው ለማንኛውም ግጭት መንስኤና ለህገ ወጥ ድርጊት አገልግሎት እንዳይውል ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ኮማንድ ፖስቱ ያሳስባል፡፡

በመጨረሻም ሕብረተሰቡ ሠላሙን ከሚያናጉ ማንኛውም ኃይሎች ሲራና የጥፋት ድርጊት ራሱን በመጠበቅና ከፀጥታ ኃይሎች ጋር ተባብሮ በመስራት የከተማውን ብሎም የአካባቢውን ሠላም የማስጠበቅ ሥራ አጠናክሮ እንዲቀጥል ኮማንድ ፖስቱ ጥሪውን ያቀርባል፡፡